**9. ምስጢርን የመጠበቅ ዲሲፕልን:-**

**(THE DISCIPLINE OF SECRECY)**

ምስጢርን የመጠበቅ ዲሲፕልን ለሰው ያደረግነውን መልካም ነገር ሌላው ሰው እንዲያውቀው ከማድረግ መቆጠብ፤ ከራስም ሆነ ከሰው ሙገሳን ፈላጊ ከመሆን መጠበቅ፤ እና ከምንቀርባቸውና ከምናውቃቸው ሌሎች አገልጋዮች ጋር ውድድርና ፉክክር ማቆም መቻል፤ በእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ ላይ በመተማመንና በመደገፍ ከእስራት ነፃ ሆኖ የመኖር ዲሲፕልን ነው::

- ምስጢርን የመጠበቅ ዲሲፕልን ከብዙኃኑ ተመልካች ይልቅ፤ አንድ እግዚአብሔር ተመልካች የሆነበት ኑሮ የመኖር ዲሲፕልን ነው!!! በእግዚአብሔር አብ÷ በእግዚአብሔር ወልድ÷ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ህላዎት ውስጥ የመኖር ዲሲፕልን ነው!!!
- ምስጢርን የመጠበቅ ዲሲፕልን ሰዎች ተቀበሉት አልተቀበሉት÷ ወደዱን አል ወደዱን÷ የነብይነት ቃል የመናገርና የመኖር ዲሲፕልን ነው!!! በሰዎች ፊት ተቀባይነትንና መወደድን ለማግኘት ስንል በተናጠ ልብ ከማነብደድ ይልቅ፤ ለእግዚአብሔርሐሳብ የመገዛትና እርሱ እንደሚያይና እንደሚያውቅ እየተረዳን በፊቱ የመኖር ዲሲፕልን ነው::
- ምስጢርን የመጠበቅ ዲሲፕልን የወንጌል መጋቢነት አደራ ምስጢር÷ የቤተ ክርስቲያን ምስጢር÷ እና የግለሰቦችና የቤተሰቦች ምስጢር÷ ፈቃድ ካላገኘን በስተቀር÷ ለራሳችን የመጠበቅ ዲሲፕልን ነው!!!

**10. የአምልኮ ዲሲፕልን:-**

**(THE DISCIPLINE OF WORSHIP)**

የአምልኮ ዲሲፕልን እግዚአብሔርን ማዕከልና መዳረሻ አድርጎ በመውሰድ የእውነት መንፈስ በሆነው በመንፈስ ቅዱስ አመራር ሥር ሆኖ ለተገለጠልን የእግዚአብሔር ቃል ምላሽ በመስጠት ለጌታ ኢየሱስ ጌትነት እየተገዛን የምንኖረው የሕይወት ዲሲፕልን ነው:: እግዚአብሐርን በአምልኮ መንፈስ ውስጥ ሆነን ለማምለክ ውስጣችንን የሚያነሳሳና የአምልኳችንም ይዘት የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይገባዋል:: አምልኳችን በእውነት ላይ የተመሠረተ ካልሆነ አጉል ስሜታዊነት ስለሚሆን መሪዎች÷ ፓስተሮችና አገልጋዮች ከመድረክም ይሁን ከመድረክ ውጭ የእግዚአብሔርን ቃል

በነጠረ ሁኔታ ሊሰብኩና ሊያስተምሩ ይገባል። የስብከታቸውም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ገለፃ (EXPOSITORY PREACHING) ቢሆንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ለቃሉ ትልቅ ቦታ እንዲሰጥና በራሱም ለማጥናት እንዲጠማና እንዲነሳሳ ያደርገዋል።

❖ የአምልኮ ዲሲፕልን እንደ መሪዎች በሕይወታችን እየጠለቀ እንዲመጣ ከፈለግ ን እግዚአብሔርን በፈጣሪነቱ እና በአዳኝነቱ ማምለክ መቻል አለብን።

✓ *"ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህ ም ሆነዋልና ፥ ተፈጥረውማልና ክብር፥ ውዳሴ፥ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል።"* (ራዕይ 4፥1-11)

✓ *"መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ፥ ማህተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፤ ታርደሃልና ፤ በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ፥ ከቋንቋም ሁሉ፥ ከወገንም ሁሉ፥ ከ ሕዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሣሉ።"* (ራዕይ 5፥1-15)

እግዚአብሔርን በፈጣሪነቱ ማምለክ፥ የእጁ ሥራ የሆነውን ፍጥረቱን (ከራሳች ን አፈጣጠር ጀምሮ፥ እንስሳትን፥ እፀዋትን፥ ከዋክብትንና ብርሃናትን) እያየን በመ ደነቅ የእግዚአብሔርን ልአላዊነት ማክበር በጣም አስፈላጊ ነው። (መዝ. 136፥1-9) በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን በአዳኝነቱ ስለ ሰጠን ቤዛነት ማምለክ፥ በማድነ ቅ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያገኘነውን ደህንነት፥ የተሰጠን ምሕረትና ጸጋ፥ የማዳን ኃይሉና ችሎቱ በማሰብ ልናመልከው ይገባል። (መዝ. 136፥10-26)

❖ የአምልኮ ዲሲፕልን ሁለት ዓይነት ገጽታዎች አሉት። አንድም የግል አምልኮ አለ፤ አንድም ደግሞ የሕብረት አምልኮ አለ። (መዝ. 63፥1-11፤ 95፥1-7፤ 100፥1-5፤ 149፥ 1-9)

❖ የአምልኮ ዲሲፕልን በመሰረቱ በሳምንት በየእሁዱ የምናደርገው ወይንም በግላችን ም በየማለዳውና በየምሽቱ የምናደርገው በቀንና በጊዜ የተመጠነ ሳይሆን፤ በየዕለቱ በየትኛውም ቦታ ሕይወታችንን በእግዚአብሔር ፊት እንደ ውሃ የሚፈስበትና በሐሳ ብ ሂደታችን፥ በኑሮአችን፥ በንግግራችን፥ በድርጊታችን ሁሉ ጌታን የምናስከብርበ ት የሕይወት ዘይቤ ነው።

❖ የአምልኮ ዲሲፕልን በተለይም በሕብረት የምናደርገው አምልኮ ሁሉንም የሚያካት ት፥ ድንበር የለሽና በቋንቋ ያልተገደበ ሊሆን ይገባዋል። ስለዚህም በሕብረት የምና ደርገው አምልኮ በብዙ ማስተዋል መደረግ ስላለበት የሚከተሉትን ነገሮች ማሰባችን በጣም አስፈላጊ ነው።

- ✔ "በአንድ ልብ ሆናችሁ..."
- ✔ "በአንድ አፍ እግዚአብሔርን... ታከብሩ ዘንድ"
- ✔ "በአንድ ሐሳብ መሆንን ይስጣችሁ።" (ሮሜ 15÷5-6)
- ◆ የአምልኮ ዲሲፕልን ሥርዓት ከመፈፀም ይልቅ÷ ሕይወትን በእግዚአብሔር ፊት ማፍሰስን፤ ከስሜት ግልቢያ ይልቅ÷ በብዙ ማስተዋል ጌታን ማክበርን፤ ከቅርፅ ወይም ፎርም ይልቅ÷ ይዘትን፤ አዕምሮ በጐደለው ሁኔታ ስሜትን ከመግለፅ ይልቅ÷ በጌታ ፍርሃት ውስጥ መሆንን፤ ከሃይማኖተኝነት ይልቅ÷ የመንፈስ ቅዱስን ሕይወት ሰጪነት የምንለማመድበት ልዩ ዕጻሎት ነው!!!
- ◆ የአምልኮ ዲሲፕልን በጥንት ዘመን ከነበሩት አባቶች መካከል ጆን ዌስሊ (MONDAY JANUARY 1, 1739) በተናገረው ሐሳብ ማጠቃለል እፈልጋለሁ። *"በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ፊት ፍርሃት÷ መንቀጥቀጥና÷ መደነቅ!"*

## 11. የጸሎት ዲሲፕልን፦
## (THE DISCIPLINE OF PRAYER)

የጸሎት ዲሲፕልን እግዚአብሔር እኛን ለመለወጥ የሚጠቀምበትና ጸጋውን የሚያፈስበት÷ የመንፈስ ቅዱስንም ኃይል የምናገኝበት ልዩ የተባረከ ዓለም ነው!!! (ዕዝራ 9፤ ነህምያ 9፤ ዳንኤል 9) በጸሎት ኃይል የታሪክ ሂደት ተለውጧል፤ አዋጅ በአዋጅ ተሽሯል፤ የእግዚአብሔር ድንቅና ተአምራት ተገልጿል፤ ጨለማው ተገፏል፤ የበሽታ ኃይል ተሰብሯል፤ እዚህ ግቡ በማይባሉ ሰዎች በአሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ዓለማት በወንጌል ተገልብጠዋል፤ የጌታ ክብርም በዓለም ዙሪያ እንዲያን ጸባርቅ ምክኒያት ሆኗል!!! (የሐዋ. ሥራ 2÷41-42፤ 3÷1-10፤ 4÷23-31፤ ወዘተ.)

- ◆ በአመራር ላይ ያለን መሪዎች ሁሉ የጸሎት ዲሲፕልን ማሳደጋችንና የጸሎት ዓለም ውስጥ መግባታችን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።
- ✔ ማርቲን ሉተር፦"ብዙ ሥራና አገልግሎት ስላለኝ በየቀኑ ለሦስት ሰዓት በጸሎት ማሳለፍ አለብኝ።" ለሉተር የሕይወቱና የአገልግሎቱ አንቀሳቃሽ ሞተር የጸሎት ኃይል እንደሆነ ስለገባው÷ ብዙ አገልግሎት ባለው ቁጥር የጸሎቱ ጊዜም የበዛ ነበር፤
- ✔ ጆን ዌስሊ፦ "እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ ካልሆነ በስተቀር ምንም አያደርግም።" ከዚህ ከነበረው ርትዕ የተነሳ በየቀኑ ሁለት ጊዜ በጸሎት ያሳልፍ ነበር።

✓ አዶኒራም ጃድሰን፡- ከነበረው የግል ንግድና ካምፓኒ እያቆመ በየቀኑ ለሰባት ጊዜ ለመጸለይ ራሱን ለብቻው ይለይ ነበር::

✓ ሬይንሆልድ ነይብሁር (1892-1971 ዓ. ም.)፡- "ጌታ ሆይ፥ ለመለወጥ የማልች ላቸውን ነገሮች ለመቀበል የምችልበትን እርጋታ፥ ለመለወጥ የምችላቸውን ነገ ሮች ለመለወጥ እንድችል ብርታትን፥ ልዩነቱን ለማስተዋል እንድችል ደግሞ ጥበብን ስጠኝ::"[71]

❖ የጸሎትን ዲሲፕልን እንድናሳድግ ከፈለግን የጸሎታችን ይዘት የሚከተሉትን ሰባት ነገሮች ማካተት አለበት ብዬ አምናለሁ፡-

1. ውዳሴ (PRAISE)፡- የእግዚአብሔርን ጽድቅ፥ ታላቅነት፥ ግርማ ሞገስ ፍርድና ምህረቱን አስበን ስለ እግዚአብሔርነቱ ማወደስ፤
2. ምስጋና (THANKSGIVING)፡-
የእግዚአብሔርን ውለታ፥ ያደረገልንን ነገሮች በዘመናችን የሰራቸውትአምራቶ ች፥ በየቀኑ ስለሚያደርግልን ጥበቃ እና ስለ ቸርነቱ ውለታን በመቁጠር ማመስ ገን፤
3. ንስሀ (CONFESSION)፡- በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን በመመርመ ኃጢያታ ችንን (SIN)፥ በደላችንን (TRANSGRATION)፥ እና አመፃን (INIQUITY) በመናዘዝና በተግባር በሚገለጥም መመለስ ንስሀ መግባት፤
4. ጸሎት (PRAYER)፡- በየዕለቱ የሚያስፈልጉንን ጉዳዮች በጌታ ፊት ማቅረብ፤
5. ምልጃ (INTERCESSION)፡- ሕይወት ምንም ጊዜም ከእኛ ያለፈ መሆን ስላለ በት፤ ከራሳችን አልፈን ስለ ሌሎች ግለሰቦች፥ ቤተሰቦች፥ የቤተ ክርስቲያን አገ ልጋዮች፥ ወንጌል ላልሰሙትና ላልደረሳቸው ሕዝቦች፥ ወዘተ. መማለድ፤
6. ልዩና የጠለቀ የምልጃ ጸሎት (SUPPLICATION)፡- ይህ የምልጃ ጸሎት በጣም የተለየና የጠለቀ ሆኖ፥ ልዩና በጣም ጥልቅ ጉዳዮች ላይ (ስለ ግላችን፥ ቤተሰባ ችን፥ ቤተ ክርስቲያናችን፥ ወይንም አገራችን) ትኩረት ባለውና በብዙ እምባ በእግዚአብሔር ፊት የምናቀርበው የምልጃ ጸሎት ነው::
7. አደራ መስጠት (CONSECRATION)፡- እራሳችንን፥ ቤተሰባችንን፥ አገልግሎ ታችንን በጌታ ፊት ለጥበቃው፥ ለቸርነቱ፥ ለምሪቱ፥ ለኃይል ሰጪነቱ፥ አደራ አሳልፎ መስጠት::

---

[71] Reinhold Niebuhr (1892-1971 A.D.) - www.wikipedia.org/wiki/Serenity-Prayer. (accessed July 23, 2013).

### 12. የእርጋታ ዲሲፕልን-

### (THE DISCIPLINE OF CALMNESS) ፦

የእርጋታ ዲሲፕልን ከማየታችን በፊት ጥድፊያ ምን እንደሆነ ማየታችን አስፈላጊ ነው:: "ጥድፊያ" ከመጠን በላይ የተለጠጠ ችኮላ፥፤ ከፍርሃት፥ አቅም እንደሌለ ከማሰብ፥ ወይንም ከሀሊና ወቀሳ የተነሳ ነገሮች አሁኑኑ መደረግ እንዳለባቸው ማሰብ የመጠዳደፍ መንፈስ ነው:: ከዚህ ይልቅ የእርጋታ ዲሲፕልን መንፈስንና ልብን በማረጋጋት እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ እንዳለ በማሰብ፥ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሆኖ፥ በተሰበሰበና በረጋ መንፈስ ነገሮችን በማስተዋል የማድረግ ዲሲፕልን ነው::

- ያለ መጠዳደፍ ለመኖር መወሰን::
- ዋናዎቹ መደረግ ያለባቸውና የሕይወትና የሞት ጉዳይ የሆኑ ነገሮች በሁለተኛ ደረጃ መታየት ካለባቸው ጉዳዮች መለየት::
- "ማድረግ አለብኝ" የሚለውን አሰራር መለወጥ:: ምንም ላለማድረግም አትፍራ/ አትፍሪ::
- "አይሆንም/ አልችልም" ማለትን እወቅበት/ እወቂበት::
- "ሁልጊዜ በአገልግሎት ወይም በሥራ መጠመድ አለብኝ" የሚለውን አስተሳሰብ እና መብረክረክ አስወግድ::
- በምታደርጋቸው ነገሮች ሁሉ እውነተኝነት ያለው አመለካከት ይኑርህ::
- እግዚአብሔር ምንም ጊዜ ቢሆን ከአቅምህ በላይ የምትወጠርበት አገልግሎት ወይም ሥራ አልሰጠህም::
- በአገልግሎት በጣም ስትበካከን "አስፈላጊ" እንደሆንክ አታስብ::
- ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር በመንግሥቱ ውስጥ ልትሞላውና ልትፈጽመው የሰጠህ አደራ መሆኑን አትርሳ:: (ማቴ. 6፥33-34)

## II. አገልጋይነትና አመራር፦

## (SERVANTHOOD LEADERSHIP)

- *"እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ::"* (ሉቃስ 22፥27)

❖ *"ከእናንተ የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል። ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድም ሁሉ ከፍ ይላል።"* (ማቴ. 23፥11-12)

❖ *"ከእኔ ተማሩ፤ እኔ የዋህ፥ በልቤም ትሁት ነኝና።"* (ማቴ. 11፥29)

❖ *"የአህዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሰለጥኑ ታውቃላችሁ። በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባርያ ይሁን፤ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ፥ እንዲያገለግሉት አልመጣም።"* (ማቴ. 20፥25-28)

❖ *"እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብኩ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ... እኔ ለእናንተ እንዳደርኩ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።"* (ዮሐ. 13፥14-15)

<u>የአገልጋይነት መንፈስ ኖሮን በአመራር ላይ ለመቀመጥ ዋና ቁልፉ ያለው የልባችንን ንጽሕናና ድንግልና ለመጠበቅ የመቻላችን ጉዳይ ነው</u>። በንጉሥ ሳዖልና በንጉሥ ዳዊት መካከል የነበረውን ልዩነት ያመጣው ዋናው ነገር የልባቸው ጉዳይ ነበር። ሳዖል ለንግሥና ሳይቀባ ልቡን ያከበደውና ሐሳቡን የያዘው ነገር "የአህዮች ፍለጋ" ጉዳይ ነበር። እንዲያውም ነቢዩ ሳሙኤልም ስለዚህ የከበደው ነገር ለሳዖል ትምቢት መናገር ነበረበት። (1ሳሙ. 9፥20) በአንፃሩ ዳዊት ለንግሥና ከመቀባቱ በፊት ልቡን የያዘው "የእግዚአብሔርን ፊት" የመፈለግ ጉዳይ ነበር። እንዲያውም ዳዊት በመዝሙር 27፥ 4፥ 8) ላይ፦ *"እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንኩት፥ እርሷንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፥ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ... አንተ ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ፥ አቤቱ ፊትህን እሻለሁ፤ ልቤም አንተን አለ።"*

በመጨረሻም ሳዖል ከንግሥናው ለመውረድና እግዚአብሔር እስኪንቀው ድረስ ያደረገው ጉዳይም "የአህዮች ጉዳይ" ነው። (1ሳሙ. 15፥17-23) በአንጻሩ የንጉሥ ዳዊት ፍጻሜ ከመጀመሪያው ልቡ በተያዘበት በእግዚአብሔር ሐሳብ ነው የደመደመው። "እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ፥ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ።" (የሐው. ሥራ 13፥22) "ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ።" (የሐዋ. ሥራ 13፥36)

በአመራር ላይ ያሉ መሪዎች ሁሉ ሊጠይቁት የሚገባ ጥያቄ፦ "አገልጋይ መሪ ነኝ፥ ወይንስ ሌሎች እንዲያገለግሉኝ፥ እንዲገዙልኝ የምፈልግ መሪ ነኝ?!" የሚለው

ን ነው:: በፍጹም ሐቀኝነት ይህንን ጥያቄ ለመመለስ መቻል አለመቻላችን በልባችን ያለውን ዝንባሌ (INTENTION) እና መንስኤ (MOTIVE) የሚያንጸባርቅ ነው:: "አገልጋይ መሪ"፥ ወይንም "መሪ አገልጋይ" መሆናችንን መመዘኛ የሚሆኑ ብዙ መንገዶች ቢኖሩም፣ ጥቂቶችን ለመግለጽ እሞክራለሁ::

## ሀ. "አገልጋይ መሪ" ወይንስ "መሪ አገልጋይ"?

1. አንደኛው:- አገልጋይ መሪ ወይንም በአመራር ላይ ስለተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል መሆናችንን መመዘኛው ሰዎች ለሚሰጡት አስተያየት (FEEDBACK) የሚኖረን አቀባበል ነው:: ራሱን ለመገልገል የሚፈልግ፥ መሪ ስለሆነ ብቻ ለማገልገል የሚቀናው ነው:: ሌሎች ሰዎች በሚሰጡትም አስተያየት ያለውን ሥልጣን የተቀናቀኑ ስለሚመስለው በጣም ያዝናል፥ ወይ ይፈራል፥ ወይንም ደግሞ አጠፌታውን ለመመለስ ይሞክራል:: እንዲህ ዓይነት መሪ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጠፋው የራሱን ሥፍራ (STATUS) በመጠበቅና ስለ ስሙም በመሟገት ስለሚሆን፣ ሰዎች ለሚሰጡት አስተያየት አሉታዊ ምላሽ ይሰጣል:: ምክኒያቱም ሌሎች ሰዎች በአገልግሎቱ አስተያየት መስጠታቸው አመራሩን የማይፈልጉ ስለሚመስለው ነው::

አገልጋይ መሪ ግን ለመሪነት የተሰጠው ጸጋ ሌሎችን ለማገልገልና እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሲል የክርስቶስን አካል ለማነጽ እንደ ተሰጠው ያውቃል:: ስለዚህም ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት እርሱ ያላየውን ለማየት የሚያስችልና አመለካከቱን የሚያሰፋ መሆኑን በመገንዘብ በአዎንታዊ ምላሽ ይቀበለዋል::

2. ሁለተኛ:- በአመራር ስለ ተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል መሪ የእርሱን አገልግሎት የሚተካ ሰውና ትውልድ ለማዘጋጀት ያለውን ፈቃደኝነት በመመልከት ነው:: መሪ አገልጋይ ለሥልጣን፥ ለኃይል፥ ለመታወቅና ዝነኛ ለመሆን ካለው ፍላጎት የተነሳ የሚመጣው ሰው ቦታውን የሚያስለቅቅና ቢያንስ የእርሱን ገጽታ የሚጋርድ ስለሚመስለው፣ እርሱን የሚተካ ሰው ለማዘጋጀት ምንም ዓይነት ፍላጎት የለውም:: የእግዚአብሔር ሕዝብም የእርሱ አገልግሎት ተጠቃሚ አድርጎ በመያዝ በሕዝቡ ውስጥ የተቀመጠውን እምቅ ስጦታ ፈልቅቆ ለማውጣትና አገልጋዮችም እንዲነሱ ለማውጣት ጉልበት የለውም::

አገልጋይ መሪ ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ ያለውን እምቅ ስጦታ ቢያድግና ተፈልቅቆ ቢወጣ ብዙ አገልጋዮች ከመካከሉ ሊነሱ እንደሚችሉ ስለሚያስተው

ል፤ ከእርሱ የተሻለ ትውልድ እንዲነሳ ምክኒያት ሆኖ ለመገኘት ይተጋል:: ከሕዝቡም መካከል አገልጋዮችና መሪዎች እየተነሱ በሚያይበት ጊዜ ሐዋሪያው ጳውሎስ አብረውት ስለሚያገለግሉ ሰዎችና ጌታ ስላስነሳቸው መሪዎች "*ስለ ወንድሞቻችን የሚጠይቅ ቢኖርም የአብያተ ክርስቲያናት መልዕክተኞችና የክርስቶስ ክብር ናቸው::*" (2ቆሮ. 8÷23) እንዳለው፤ በእነርሱ መነሳት ደስታው ከመጠን ያለፈ ነው:: ጸጋቸውንም ለማሳደግ ሕይወቱን በእነርሱ ላይ ያፈሳል:: የሚተካው ትውልድ በማግኘቱም ሐሴት ያደርጋል፤ በሕይወት እያለ ሌላ ትውልድ መነሳቱ ክብር እንደተጨመረለት ያስባል::

3. ሦስተኛ፡- በመሪነት ስለተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል መሪ ለውስጣዊ ውበት ወይንም ለውጫዊ የግል ገጽታ የሚሰጠውን ቦታ ለማየት ልንመዝነው እንችላለን:: በአመራር ላይ ስለ ተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል መሪ አብዛኛውን ጊዜ ራሱ በራሱ÷ ወይንም ሰዎች በሚሰጡት ጎሸታ ይረካል:: በራሱና በሰዎች ለመመስገን አጥብቆ ይፈልጋል:: የውጫዊ የግል ገፅታ በጣም ስለሚያስጨንቀው÷ በውጭ በሚያደርጋቸው "መልካም ድርጊቶች" ብቻ ስለሚረካ÷ እግዚአብሔር የሚያየውን የውስጡን ንጽህናና የሐሳቡን ድንግልና ለመጠበቅ አይጥርም:: በተጨማሪም የእርሱ ተመልካች ብዙኃን ስለሆኑ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ መልክ እያሳየ መኖር ይወዳል:: ከዚህ የተነሳ ሰዎች ማንነቱን ለማወቅ ይቸገራሉ::

አገልጋይ መሪ ግን አንድ ወጥ የሆነ ሰው ስለሆነ÷ በእግዚአብሔርም ይሁን በሰዎች ፊት ያለው መልክና ገፅታ አንድ ነው:: የእርሱ ተመልካች አንድ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ÷ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት የሚያደርገው ጥረት የለውም:: በውጭ ከሚያደርጋቸው ድርጊቶች ይልቅ፤ ለውስጣዊ ውበት÷ ዝንባሌ÷ እና መንስኤ ልዩ ትኩረት ይሰጣል!!!

4. አራተኛው፡- በመሪነት ስለ ተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል አገልጋይ ለመገምገም የሚረዳን ስኬታማ ለመሆን የሚያደርገውን ጥረት በማየት ነው:: በመሪነት ስለ ተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል መሪ የሚረካውን የሕይወቱ ዓላማ አድርጎ የሚነሣው ስኬታማ መሆንን ነው:: ስለዚህ የእርሱ ትኩረት ከጥራት ይልቅ ብዛት፤ ከሕይወት ንጽሕና ይልቅ፤ የአገልግሎት ውጤት፤ ሕይወት በሌሎች ሰዎች ከመዝራት ይልቅ፤ የፕሮግራሞች መካሄድን፤ ከጥቂት ሰው ጋር ስባዊ ጨዋታ ይልቅ፤ ከብዙ ሰዎች ጋር መደባለቅን፤ ዘላለማዊ ሥርጸት ከሚያመጣ ነገር ይልቅ፤ ጊዜያዊ በሆነ ገለባና ፍሬ

በሌለው የአገልግሎት ክምር (የሣር÷ የእንጨት ወይም የአገዳ ክምር- 1ቆሮ. 3:12) በማተኮር ስኬታማ ለመሆን ይታገላል::

አገልጋይ መሪ ግን ከስኬታማነት ይልቅ፤ ታማኝነት፤ ከብዛት ይልቅ ጥራት፤ ከአገልግሎት ውጤት ይልቅ በአገልግሎቱ ሂደት ውስጥ ያለው ንፅህና፤ ከፕሮግራም ቅንጅት ይልቅ ሕይወትን መዝራት፤ ከጊዜያዊ ጎሽታ ይልቅ፤ ዘላለማዊ የሆነ ለውጥ፤ ስኬታማ እንደሆነ ለማሳየት የሚደረግ ከክምር አገልግሎት ይልቅ፤ "በወርቅ÷ በብር፤ በከበረ ድንጋይ" እንደተባለ (1ቆሮ. 3:12) አገልግሎ ማለፍን ይመርጣል::

5. አምስተኛው:- በአመራር ላይ ስለተቀመጠ ብቻ የሚያገለግል መሪ አገልጋይ ለማየት የሚረዳን ለሚያጋጥሙት ፈተናዎች የሚሰጠው ምላሽ በመገንዘብ ነው:: መሪ አገልጋይ አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ሳይሆን ለሕዝቡ ጆሮ የሚጣፍጠውን እየፈለገ ስለሚናገር በሕዝብ የሚመራ ሰው ነው:: የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማስፋፋት ይልቅ በሕዝቡ አዕምሮ ለመሥረፅ ለራስ ከመሳሳት የተነሣ ስለሚያገለግል እውነትን የመሸራረፍ ባህርይ አለው:: በተጨማሪም የእርሱ አገልግሎት እንደሰናፍጭ ቅንጣት ቀስ በቀስ ከሚያድግ የተደላደለ አግልግሎት ይልቅ ዝነኛነትንና ታዋቂነትን ስለሚፈልግ አንድ የሆነ "የሚያስደንቅ ተአምር" እንዲሰራ ይመኛል:: ከዚህም ሌላ የበላይ ለመሆን ካለው ብዙ ፍላጎት የተነሣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ "ተከታይና ተጠቃሚ" በማድረግ ሥልጣኑንና ኃይሉን ያለ አግባብ ይጠቀም በታል::

አገልጋይ መሪ ግን በዘመኑ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሐሳብ አገልግሎ ለማለፍ ስለሚፈልግ በሰዎች ለመወደድ የሚያደርገው ጥረት የለውም:: እየታየ የማይታይ መሪ ስለሆነ ታዋቂና ዝነኛ ለመሆን ፍላጎቱም የለውም:: እግዚአብሔር ሕዝቡን በአደራነት የሰጠው መሆኑን ስለሚያውቅ የሕዝቡ ስብዕና ክብር በሚጠብቅ መልኩ እንደየዕድሚያቸው አክብሮ መያዝና እርሱንም ማገልገል ዋና ዓላማው ነው::

### ለ. የአገልጋይ መሪነት መመሪያዎች:-

ሮበርት ኬ ግሪንሊፍ የሚባለው አስደናቂ የሆነ ጸሐፊ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተማራቸውን ነገሮች መሠረት በማድረግ ስለ አገልጋይ መሪነት መጽሐፍ ጽፏል:: የዚህ መጽሐፍ ዋና ዋና ሐሳቦች በተጨመቀ መልኩ እንደሚከተለው አቅርቤአቸዋለሁ::

“1. አገልጋይ መሪዎች ሰዎችን ማድመጥ ብቻ ሳይሆን የመስማት ችሎታ አላቸው:: ሲሰሙም በእርጋታና በጥሞና ከመስማታቸውም ሌላ፣ በቃል የተባለውን ብቻ ሳይሆን በቃል ያልወጣውን በመሥመሮች መካከል ያለውን ሐሳብ መስማት ይችላሉ::

2. አገልጋይ መሪዎች ሰውን የመረዳት፣ የመቀበልና በርኅራኄ ዓይን የማየት ባሕርይ አላቸው:: ሰው ያለበትን ችግር፣ መከራና ስቃይ ተመልክተው ራሳቸውን በሁኔታ ውስጥ ማመሳሰል፥ ለመረዳትም የተዘጋጀ ልብና መንፈስ አላቸው::

3. አገልጋይ መሪዎች የራሳቸውን ቁስል/ ሐዘን ለሌሎች ለማካፈል የተከፈተ ልብ አላቸው፣ የሌሎች ሰዎችን ቁስል/ ሐዘን እንዲፈወስም ሙሉ ልባቸውን ሰጥተው ለመፀለይ የሚችሉበት ልዩ ቅንነት የተሞላበት መንፈስ አላቸው::

4. አገልጋይ መሪዎች እግዚአብሔርን ከማወቃቸው የተነሣ ራሳቸውን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ድካማቸውን ውሱንነታቸውን፣ ያላቸውን አቅምና የተሰጣቸው የጸጋ ስጦታ ምን እንደሆነ ልዩ መረዳት አላቸው::

5. አገልጋይ መሪዎች የሥልጣን እርከናቸውን ተጠቅመው ሰዎችን ለማሳመን ከመሞከር ይልቅ፣ በፅድቅ ኑሮአቸውና ትህትና በተሞላው የአመራር ስጦታቸው ሰዎችን የማሳመን፣ ሰዎችን አምነውበት እንዲቀበሉት የማድረግ ልዩ ስጦታ አላቸው::

6. አገልጋይ መሪዎች በየቀኑ ከሚደረገው ጥቃቅን ነገር አልፈው ትልቁን ስዕል፥ እና ትላልቅ ህልሞች ማየትና ማለም ይችላሉ:: ይህንን ሲያደርጉ ግን በየዕለቱ የሚሠራውም በብቃትና በጥራት ለመፈፀም እጅግ ይተጋሉ፣ የትኩረት አቅጣጫም ያላቸው መሪዎች ናቸው::

7. አገልጋይ መሪዎች አርቆ የማየት ችሎታ አላቸው:: ካለፈው ዘመን የተማሩትን ያስተውላሉ፣ በአሁኑ ዘመን ያለውን እውነታ ይገነዘባሉ፣ ለሚቀጥሉት ዓመታት የሚሆነውን ጉዳይ ሲወስኑም ሊያመጣ የሚችለውንም ሰበብ የማስተዋል ችሎታ አላቸው::

8. አገልጋይ መሪዎች ባለ አደራዎች እንደሆኑ ስለሚያውቁ የክርስቶስን አካል ደህንነት ለመጠበቅ እግዚአብሔር በሰጣቸው ፀጋና ኃይል መጠን በትጋት ያገለግላሉ::

9. አገልጋይ መሪዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ በግል ህይወቱ በመንፈሳዊ አቅጣጫና በኑሮም እያደገ እንዲመጣ በሁሉ መንገድ እያደገና እየጎለበተ እንዲመጣ የተሰጡ ናቸው::

10. አገልጋይ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ያለው ሕዝብ እንደ አንድ ሕብረተሰብ እያደገና እየጥነከረ እንዲመጣ፤ አካባቢያቸው ካሉት አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር የተለየና የቀረበ ግንኙነት መሥመር ይከፍታሉ፤ ያጠነክራሉም::"[72]

**ሐ. ማጠቃለያ ሐሳቦች:-**

በአመራር ላይ ስንቀመጥ ከሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች መካከል ትዕቢትና ፍርሃት ናቸው:: ትዕቢትና ፍርሃት የሕይወታችንና የአገልግሎታችን ማዕከል፥ የአምልኮታችንም እምብርት፥ የማንነታችንም ዋስትና፥ ዋናው ብቸኛ ተመልካችና የመጨረሻው ፈራጃችን እግዚአብሔር ከሚሆን ይልቅ፤ በሌሎች ነገሮች እንድንተካው ያደርጉናል:: ልባችን በትዕቢት ሲወጠር የራሳችንን ክብር ማንጸባረቅ፤ ለተደረገውም ነገር ሁሉ ክብሩን መውሰድ፤ የሌሎች ሰዎች ጆሮ እኛን ብቻ እንዲያደምጥ የሚያስገድድ ሰው መሆን እንጀምራለን:: በፍርሃት የተዋጡ መሪዎች ካሉት የሥልጣን ቦታ በስተኋላ የመደበቅ፤ ኢንፎርሜሽን የማፈንና ሌሎችን ሰዎች በመቆጣጠር እንዲበረግጉ የማድረግ ባሕርይ አላቸው:: ትዕቢትና ፍርሃት ምንም ጊዜም ከእግዚአብሔር፤ ከሌሎች ሰዎችና ከራሳችንም እንድንሸሽ ያደርገናል:: ከዚህም ሌላ፥ ስለ ራሳችንም ሁኔታ የተሳሳተ አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል:: (ምሳሌ 13:10፤ 16:5፤ 16:18፤ 25:14፤ 25:27፤ 27:2፤14:21፤ 1ቆሮ. 4:7 ምሳሌ 22:4፤ 18:16፤ 21:20፤24:-4) ትዕቢትና ፍርሃት መሪውን ብቸኛና የተነጠለ፤ እውነትን መቀበልና መጋፈጥ የማይችል፤ ያደርገውና፥ ሌሎችን ሰዎች በመስማት የሚገኘውን የከበረ ሐሳብና ምክር እንዳያገኝ ያግደዋል::

ከዚህ ይልቅ አንድ መሪ በመጀመሪያ አገልጋይ መሆን አለበት:: የመጀመሪያውን መጀመሪያ ማድረግና የሕይወት ቅደም ተከተሉንም ማስተካከል ይገባዋል:: (ማቴ. 6: 33) ስለዚህ ከትዕቢትና ከፍርሃት ይልቅ፥ ትሕትናና እርግጠኝነትን፤ ከመነጠል ይልቅ፥ ከሕዝቡ ጋር አብሮ ለመሆን መፈለግን፤ ከጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ ዘላለማዊ ብድራት እንዳለ ማሰብን አጥብቆ ሊከተል ይገባዋል:: አገልጋይ መሪ የተጠራበት ጥሪ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለበትና ክቡር ጥሪ መሆኑን ተገንዝቦ፤ በመታዘዝ፤

[72] Robert K Greenleaf, *Servant Leadership,* (New York: Paulist Press, 1977).

በመስጠትና በመስዋዕትነት ሊያገለግል ይገባዋል። እንዲህ ዓይነት ሕይወት ለመኖር ና ንጽሕና፣ ቅንነት እና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት ለማገልገል ለእግዚአብሔር ም ሆነ ለሰው ተጠያቂነት ያለው ግንኙነት መፍጠር አለበት።

1. በውስጡ የሚነሳውን ስውር ትዕቢት ታማኝነት የሌለው "ስኬታማነት" የሚመኘው ልብን ለመግራትና ለመገራት ክፍት መሆን።

2. በእግዚአብሔር ፊት የውስጥን መንስኤ (MOTIVE)፥ ሐሳብና፥ ድርጊት አቅርቦ ለመመርመርና ለመለወጥ ፈቃደኛ መሆን።

3. የጌታ ኢየሱስን አገልጋይ መሪነት ምሳሌነት በመከተል የእርሱን መልክ የመሰለ ለመሆን መቁርጥ።

4. ያለ ፍርሃት የራሱን ንፁህ ያልሆነ ሕይወት፣ ከአገልጋይ መሪነት ጋር የማይጣጣም ባሕርዩን ለመለወጥ መወሰን።'

5. እግዚአብሔር ስለ እርሱ የተናገረውን ድካምና ጉስቁልና ሌሎች ሰዎችም ሲናገሩት ቢያመውም እንኳ በመገረምና በትሕትና መቀበል መቻል። በእግዚአብሔ ር ፊት ተጠያቂ ከመሆኑም በተጨማሪ፣ ቢያንስ በሌላ አንድ ሰው ፊት ተጠያቂ ለመሆን መፍቀድ።

6. የመታወቅ፣ ዝነኛ የመሆን፣ ሥልጣንና ኃይልን የመጓጓት ፍላጎት፣ በስስት ምክኒያት የእግዚአብሔር ቤት ገንዘብና ንብረት ለራስ ጥቅም የማዋል፣ ጌታን ከመ ፍራት ይልቅ ሰውን በመፍራት እውነት የመሸራረፍና የመቀያየጥ ፈተናዎች ከጅም ራቸው እንዲነቀሉ በቆረጠ ልብና መንፈስ መነሣትና በራስ መጨከን መቻል።

7. በትዕቢትና በፍርሃት ምክኒያት፣ የራሱንም ስምና ክብር ለማስጠበቅ ሲል የጐዳቸውና ያሳዘናቸውን ሰዎች ይቅርታ ለመጠየቅ፣ ያደረገውንም በፊታቸው ለመ ናዘዝ መቻል። ስህተት ሲሠራም "የእኔ ጥፋት ነው" ብሎ መቀበልና ማስተካከል።

❖ <u>አገልጋይ መሪነት የሚጀምረው በቅርባችን ካሉ ሰዎች ጋር (ማለትም፡- ቤተሰባችን፥ ጓደኞቻችንና አብረውን የሚያገለግሉ አገልጋዮች) ባለን የግንኙነት ሥምረት ነው!!!</u>

# ምዕራፍ አምስት

## የአገልግሎት ጥሪ፥ ቅንዓት፥ ራዕይና መዳረሻ

## (CALLING, PASSION, AND VISION)

- *"ለአገልግሎት ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ስለ ቆጠረኝ ኃይል የሰጠ ኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን አመሰግናለሁ።*
  *(1ጢሞ. 1፡12)*
- *"... የቤትህ ቅንዓት ይበላኛል ..." (ዮሐ. 2፥ 17)*
- *"... ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራዕይ እምቢ አላልሁም።"*
  *(የሐዋ. ሥራ 26፥ 19)*

## I. የአገልግሎት ጥሪ፦

### ሀ. ትርጉመ ወሰን

የአገልግሎት ጥሪ "እግዚአብሔር እኛን ለራሱ ክብር የእርሱ ዕቃ እንድንሆን ወደራሱ ሲጠራን፤ ሁለንተናችንን፤ የምናደርገውና ያለንም ሁሉ፤ በፍፁም መሰጠት ፥ በሙሉ ኃይልና፥ ትኩረት ለወንጌል ጥሪና አደራ መለየት ማለት ነው።"[73] የአገል ግሎትን ጥሪ በተመለከተ የደቡብ አፍሪካው አርክ ቢሾፕ ዲስሞንድ ቱቱ እንዲህ ይላሉ፦

"በዓለም ላይ ሦስት ዓይነት ሰዎች አሉ፦ ነገሮች እንዲከናወኑ የሚያደርጉ፥ ነገ ሮች ሲከናወኑ የሚያዩ ተመልካች የሆኑና ነገሮች ከተከናወኑ በኋላ ክብሩን ለመውሰ

---

[73] Os Guiness, *The Call: Finding and Fulfilling Central Purpose of Your Life*, (Nashville, TN: Word Publishing Group, 1998, 2003), 29.

ድ የሚፈልጉ:: በተቻለህ መጠን በመጀመሪያው ቡድን ለመሆን ሞክር፣ ምክኒያቱም እዚያ የሚገኙት በጣም ጥቂት ናቸው::"

የአገልግሎት ጥሪ እግዚአብሔር በመለኮታዊነቱ ግለሰቦች ሙሉ ዘመናቸውን በመንግሥቱ ሥር የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲያገለግሉ ለተለየ ዓላማ የሚለዩበት የከበረ ጥሪ ነው::

- "*ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ... ለእግዚአብ ሔር ወንጌል ተለየ:: ...እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::*" (ሮሜ. 1፡1-4)
- "*በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ ጳውሎስ ...*" (1ቆሮ. 1፡1)
- "*በኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታንም ባነሣው በእግዚአብብሔር አብ ሐዋርያ የሆነ እንጂ፥ ከሰዎች ወይም በሰው ያልሆነ ጳውሎስ*" (ገላትያ 1፡1-2)

የአገልግሎት ጥሪ ባለቤትና ምንጩ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በመሆኑ "ከሰዎች ወይም በሰው" የሚመጣ አይደለም:: መለኮታዊ / አምላካዊ ጥሪ ነው:: የአገልግሎት ጥሪ ዋና ዓላማው መልዕክትና መልዕክተኛ የሆነው ወንጌል፥ ማለትም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በፍፁም መሰጠት መስበክ፥ ማወጅና፥ የምሥራቹን ለሰ ው ሁሉ መናገር፣ ጌትነቱንም በኑሮ ማሳየት፣ አዳኝነቱንም መግለጥ ነው:: ይህም የሚደረገው ሐዋርያው ጳውሎስ "*መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋርአስተ ያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ እንናገራልን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል አይደለም::*" እንዳለው (1ቆሮ. 2፡13) በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ቅባት የሚደረግ አገልግሎት ነው:: በመጨረሻም የእግዚአብሔርን ክብር በሙላት ያለመታገድ እንዲገለጥ ማድረግ ነው::

## ለ. ስለ አገልግሎት ጥሪ የተሳሳቱ አመለካከቶች:-

የአገልግሎት ጥሪ በብሉይም ይሁን በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል ስናነብ ለአገልግሎት የተጠሩ ሰዎች መኖራቸው አሌ የማይባል ሐቅ ነው::

- **በብሉይ ኪዳን፡- <u>ሌዋውያን</u>** (ዘፀ. 28፡1፣ 29፡1-9፣ 30፡22-33፣ 40፡9-16፣ 34-38፣ ዕብ. 5፡1-4)፣ **<u>ካህናት</u>** (ዘፀ. 28፡1፣ 41፣ 29፡1፣ 7-9፣ 30፡1-33፣ 40፡1-38)፣

**ነቢያት** (ሙሴ ዘፀ. 3:1-13፥ ሳሙኤል:- 1ሳሙ. 3:1-21፤ ኤልያስ:- 1ነገ. 17:1፤ ኤልሳዕ:- 1ነገ. 19:16፤ 19-21፤ ኤርምያስ:- ኤር. 1:4-10፤ ወዘተ)፤ **መሳፍንት** (ጌድዮን መሳ. 6:11-27፥ ሳምሶን:- 13:1-25፤)፤ **ነገሥታት** (ንጉሥ ሳዖል:-1ሳሙ.10:1-27፤ ንጉሥ ዳዊት:-1ሳሙ. 16:1-13)::

- **በአዲስ ኪዳንም:- አሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙርት**:- ( ማቴ. 4:18-20፤ ማር. 1:16-20፤ 3:13-18፤ ሉቃስ 5:1-11፤ ይፐሐ. 1:35-51)፤ **ሐዋርያው ጳውሎስ**:- (የሐዋ. ሥራ 9:1-31)፤ **አራቱ ቢሮዎች (OFFICES)** (ሐዋርያት፥ ነቢያት፤ ወንጌል ሰባኪዎችና እረኞችና አስተማሪዎች)፤ **ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎችም** (ሮሜ. 12:3-8፤ 1ቆሮ. 12:4-11)::

የአገልግሎት ጥሪ በተመለከተ ግን ጥግ የያዙ እና ከእግዚአብሔር ቃል የማይጣጣሙ የሰው አስተሳሰቦች እንዳሉ መጥቀሳችን አንድም እነዚህን አጉልና የማይመቹ ሐሳቦችን ለማረምና ለማስተካከል፤ ሌላው ደግሞ እውነት የሆነውን ለማስጨበጥ ይረዳል ብዬ አምናለሁ::

1. <u>አንደኛው አመለካከት "የተለጠጠ መንፈሳዊነት ያለው" (MYSTICAL SUBJECTIVISM) ነው::</u> ይህ አመለካከት ሰው እግዚአብሔር ጠርቶኛል ለማለት የሚችለው ለሐዋርያው ጳውሎስ "የብርሃን ነፀብራቅ ልምምድ" ከሰማይ ሲላክለት ብቻ ነው ብሎ ያምናል:: እንዲህ ዓይነት የተለየ ልምምድ ከሌለው ግን ጌታ ጠርቶኛል ማለት አይችልም ብሎ ያምናል:: እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ኃይልና አሠራሩ ልዩ ልዩ የጥሪ መንገዶች እንዳሉት መቀበል የማይፈልግ አመለካከት ነው:: ሌላው ችግሩ ደግሞ ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ ለልምምድ ትልቅ ቦታ ይሰጣል::

2. <u>ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ የአዕምሮ ዳሰሳ (RATIONAL OBJECTIVISM) የሞላበት የመጀመሪያውን አጉል መንፈሳዊንት ለመፃረር የተደረገ አቋም ነው::</u> ይህ አመለካከት እግዚአብሔር ሰዎች ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት አይጠራም፤ መጥራትም አቁሟል ብሎ ያምናል:: በዚህ አመለካከት ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተለየ ጥሪ የሚያስፈልገው ሳይሆን፤ ከሥራ መስኮች አንዱ አማራጭ ነው ብሎ ያምናል:: እንዲህ ዓይነት አቋም በፓስተሮችና ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተጠሩ ሰዎች ተፃራሪ ብቻ ከመሆኑም በላይ ሳያውቀውም (ወይንም እያወቀ) የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን የሚጋፋ አቋም ነው:: የእግዚአብሔር መለኮታዊ አሠራርንም ይጋፋል::

## ሐ. እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራ፡-

1. በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሚያየው የሰውን ባሕርይ ነው:: "... ሰው እን ዲያይ እግዚአብሔር አያይምና... ሰው ፊትን ያያል እግዚአብሔር ግን ልብን ያያ ል አለው::" (1ሳሙ. 16:6-13) ሐዋርያው ጳውሎስም ለአመራር የሚበቁትን መሪ ዎች መለኪያ የሚሆን መመርያ ሲጽፍ የጠቀሳቸው ሦስት ዋና ነገሮች (ወጥነት፣ ታማኝነት፣ እና ራስን መግዛት) የሰውን ባህርይ የሚያመለክቱ ናቸው:: ጌታ ኢየሱስ ም ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው መለኪያ የዚህ ሁሉ መሠረት ነው::

- "ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና..." (ማቴ. 11:29)
- "የአህዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሰለጥኑ ታው ቃላችሁ:: በእናንተስ እንዲህ አይደለም፣ ነገር ግን... " ማቴ. 20:20-28)

2. እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ የተፈጥሮ ችሎታቸውንም ይሁን፣ ወይንም ያላቸውን ዳራ (BACKGROUND) ሊጠቀምም ወይም ላይጠቀም ይችላል:: እግዚአ ብሔር አብዛኛውን ጊዜ ምንም ዓይነት አቅምና ችሎታ የሌለውን ሰው አስነስቶ መጠቀምን ይወዳል:: እንዲህ ዓይነቱን ሰው በቃሉና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አስነሥ ቶ መጠቀም ልማዱ ነው:: (1ቆሮ. 1:26-31) ጌታ የጠራቸውና ዓለምን በወንጌል ኃይል እንዲደርሱ ያስቻላቸው አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አሣ ከማጥመድ ሌላ ምንም የተወሳሰበ እውቀት ያልነበራቸውና በዘመኑ የነበረውን የትምህርት ተቋም ውስጥ ገብተው ያልተማሩና፣ ሐዋርያው ጳውሎስም "...ደካሞች፣ ... ያልከበሩ...፣ የምናፍ ርባቸው ብልቶች..." የሚላቸውን (1ቆሮ. 12:22-24) ሰውችን ነው:: (የሐዋ. ሥራ 1:11÷2:8፤ 4:13÷ 5:28) በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ዓይነት ሲጠራ "በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር፣ እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ ነበረና::" (1ቆሮ. 2:2፤13) እንዲሉና በፍፁም ትህትናና መሰጠት እንዲያገለግሉት ያደርጋቸዋል:: "ጸጋዬ ይበቃሃል፣ ኃይሌም በድካምህ ይፈጸማልና" (2ቆሮ. 12:9) ይላቸዋል::

3. እግዚአብሔር የሚጠራቸውን ሰዎች ያዘጋጃቸዋል:: ጌታ እግዚአብሔር፡-

- ዮሴፍን ለአሥራ ሦስት ዓመታት በመከራ ካነጠረውና ካሳለፈው በኋላ ሰማንያ ዓመታት ከጌታ በረከትንና ብድራትን የሚቀበልባቸው ዓመታት ከመስጠቱም ሌላ፥ አስደናቂ የሆነ አመራር እንዲመራና ጥሪውን እንዲለማመድ አድርጎታል
- እግዚአብሔር ሙሴን ሲጠራው ለአርባ ዓመታት በግብፅ ቤተ መንግሥት ሆኖ የተማረውን ትምህርት ለትዕቢት ምክኒያት እንዳይሆነው በማሰብ ለአርባ ዓመታት በምድረ-በዳ የበጎች እረኛ እንዲሆን ካሰለጠነውና ከቀረፀው በኋላ፥ ለአርባ ዓመታት የእሥራኤልን ሕዝብ አስደናቂ በሆነ አመራር እንዲመራና የተጠራበትን ጥሪ እንዲያከናውን አድርጎታል:: (የሐዋ. ሥራ 7:23፤30፤42)
- ዳዊት በአባቱ የተረሳና ለቁም ነገርም ያልታሰበ (1ሳሙ. 16:11፤ ምዝ. 27:10)፤ በወንድሞቹም የተጠላ (1ዋሙ. 17:28-29)፤ በነቢዩ ሳሙኤልም ያልታሰበ (1ዋሙ. 16:6-13)፤ በጎልያድ ዓይንም የተናቀ (1ሳሙ. 17:41-42)፤ እና በንጉሥ ሳዖል ዓይን የማይሞላና (1 ሳሙ. 17:31-33) እጅግም የተጠላ (1ሳሙ. 18:9፤12፤15፤17:29፤ 19:1፤ 22:17-19) ነበር:: በአንፃሩም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ (1ሳሙ. 16:7፤ 12-13፤ የሐዋ. ሥራ 13:22-23) በንጉሥ ሳዖል ልጅ በዮናታንም የተወደደ (1ሳሙ. 18:1-3) በእስራኤልም ሕዝብ የተወደደ (1ሳሙ. 18:7-8)፤ በአህዛብ ነገሥታት ዘንድም የተከበረ (1ሳሙ. 21:10-12፤ 29:5-6፤9) ነበር:: እግዚአብሔር ዳዊትን በብዙ መከራ ካሳለፈውና ካሳደገው በኋላ፤ ከአብርሃም ቀጥሎ ሁለተኛው አምድ የሆነ አባት እንዲሆን አድርጎታል:: (ማቴ. 1:1) ሐዋርያትም ነቢይነቱን አስረግጠዋል:: (የሐዋ. ሥራ 2:30)
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት የራሱ ሕይወትና አገልግሎት ካሪኩለም በሆነበት ልዩ ትምህርት ቤት ውስጥ አስገብቶ ለሦስት ዓመት ተኩል አሰልጥኖአቸዋል::
- ሐዋርያው ጳውሎስም ጌታ ኢየሱስ በራዕይ ከተገለጠለት በኋላ፤ ለመፀለይናየእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት በዓረብ አገር ለሦስት ዓመታት ራሱን ሰውሮ ተቀምጧል:: (ገላ. 1:15-2:2)

4. <u>እግዚአብሔር የሚጠራቸውን ሰዎች ለተጠሩበት አገልግሎት እንዲበቁ ያስታጥቃቸዋል::</u> እግዚአብሔር ከምናስበው በላይ ጥበብ የተሞላ አምላክ ስለሆነ፤ <u>መከራ ሲያመጣም እንደ አቅማችን ነው፤</u> (1ቆሮ. 10:12-13)፤ <u>ትዕዛዝ ሲሰጥም እንደ አቅማችን ነው፤</u> (ራዕይ 2:24)፤ እና <u>የጸጋ ስጦታ ሲሰጥም እንደ አቅማችን መጥኖ ነው!!!</u> (1ቆሮ. 12:11፤ ማቴ. 25:14)

## መ. የአመራር አገልግሎት ልዩነት:-

በመሪነት የሚቀመጡ ሰዎች ሁሉ በጅምላና በአንድ ዓይነት ማየቱ የሚረዳ አይ መስለኝም:: ሦስት የተለያዩ ፀጋ ያላቸው መሪዎች እንዳሉ ማወቁ የጠቅማል ብዬ አምናልሁ::

1. *ራዕይ ያላቸው መሪዎች:-* (Visionary Leaders)

እነዚህ መሪዎች የመምራት ጸጋና ችሎታ ያላቸው ከመሆኑም በላይ ወደፊት ሊደረግ የሚችለውን አርቀውና አጥልቀው የማየት ችሎታ ያላቸውና የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያድግበትና የሚጎለብትበትን አዳዲስ መንገድ የመተለም የማሳየትና የማሳመን ስጦታ አላቸው::

- <u>ትኩረታቸው</u>:- አዳዲስ የአገልግሎት በሮችን መክፈትና በሰዎች ውስጥ ያለውን እምቅ የጸጋ ስጦታ እንዲጠቀሙበት ማነሣሣት ነው::
- <u>አጠባበቃቸው</u>:- ባለው ሁኔታና እየተደረገ ባለው አገልግሎት ስለማይረኩ፤ ለውጥ መምጣት እንዳለበት ያምናሉ::
- <u>ስላሉበት ቤተክርስቲያን ሰዎች ያላቸው አመለካከት</u>:- ቤተ ክርስቲያኒቱ እያደገች ያለችና ለውጥ ለማምጣት የምትጥር ሕይወት ያላት ነች ይላሉ::
- <u>የሚጠይቁት ጥያቄ</u>:- ሰው ሁሉ በራዕይ ውስጥ ገብቷል?
- <u>አደጋው</u>:- መሪውን ታዋቂና ዝነኛ እንዲሆን ይፈትነዋል፤ ወይንም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ፖለቲካ እንዲጫወትና ራዕዩን፤ እንዲጥል ሊያደርገው ይችላል::

❖ <u>ሊጠየቅ የሚገባ ጥያቄ</u>:- የክርስቶስን የክብር ወንጌል እንዲሮጥ አድርጓል ወይ? የእግዚአብሔርን ሥራ እንዲሰፋ ምክኒያት ሆኖአል ወይ?

2. **የአስተዳደር ስጦታ ያላቸው መሪዎች:-** (Administrative Leaders)

እነዚህ መሪዎች የአስተዳደር ስጦታና ችሎታ ያላቸው መሪዎች ከመሆናቸውም ሌላ፤ በቤተ ክርስትያን ውስጥ ያለው የሰው፥ የገንዘብና የንብረት ሀብት እንደሚገባው መዋሉን ማየት፥ መገንዘብ፥ መቆጣጠርና መገምገም የሚችሉበት ችሎታ አላቸው::

- <u>ትኩረታቸው</u>:- ቅደም ተከተል ፕሮግራሞች፤ መዋቅሮችና ዘዴዎች፤

- **<u>አጠባበቃቸው</u>**፡- መለኪያዎች መጠበቃቸውና መከበራቸው እንደ ዋና ነገር ይቆጥሩታል።
- **<u>ስላሉበት ቤተክርስቲያን ሰዎች ያላቸው እይታ</u>**፡-በሚገባ የምታስተዳድር÷ ቋሚነት ያላትና የተረጋጋች ቤተ ክርስቲያን እንደሆነች ያስባሉ።
- **<u>የሚጠይቁት ጥያቄ</u>**፡- ይሠራል ወይ?
- **<u>አደጋው</u>**፡- ቤተ ክርስትያንን በውጭ እንደሚሠሩባቸው ካምፓኒዎች ወይም ድርጅቶች "ለማስተዳደር" ሲሞክሩ የክርስቶስ አካል የተለየ መሆኑን ስለማያስተውሉ መንፈሳዊ አቅጣጫውን ሊረሱና እግረ መንገዳቸውን አገልጋዮችንም ሆነ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊጎዱ ይችላሉ።
- **<u>ሊጠየቅ የሚገባ ጥያቄ</u>**፡- ከጌታ ሐሳብ ጋር ይሄዳል፤ ከመንፈስ ቅዱስ አሠራር ጋር ይስማማል? በቀኑ መጨረሻ የእግዚአብሔር ክብር እንዲገለጥ ምክኒያት ይሆናል?

### 3. የእረኝነት ጥሪና ስጦታ ያላቸው መሪዎች፡-

**(Shepherding Leaders)**

እነዚህ መሪዎች የእረኞች አለቃ የሆነውን ጌታን በመምሰል የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት/ በመጋቢነት ሆነው ለመምራት የተጠሩና የእረኝነት ጸጋቸውን በአንድ አጥቢያ ቤተክርስትያንም ይሁን ወይንም በሰፊው የክርስቶስ አካል መካከል የሚለማመዱ መሪዎች ናቸው።

- **<u>ትኩረታቸው</u>**፡- ሕዝብን ማነፅና መገንባት፤ ሰዎችን በፍቅር÷ የአካሉን ሕብረት ማጠናከር÷ መጠበቅና እንግዶችን የመቀበልና የማስተናገድ።
- **<u>አጠባበቃቸው</u>**፡- ሰው ለእነርሱ ክቡር ነው። ስለዚህም ግለሰብን፤ ቤተሰብንና ሕዝብን ማገልገል ዋና ጥሪያቸው ነው።
- **<u>ስላሉበት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ያላቸው አመለካከት</u>**፡- የሰዎችን ውስጣዊ ፍላጎት የምታሟላ ቤተ ክርስቲያን አድርገው ያይዋታል።
- **<u>አደጋው</u>**፡- የሰዎችን ፍላጎት በማሟላት ሰውን ደስ ለማሰኘት የሚያጎበድዱና ለመወደድ ፈላጊ ሊያስደርጋቸው ይችላል።
- **<u>ሊጠየቅ የሚገባ ጥያቄ</u>**፡- የሰዎች ሕይወት ተለውጧል? ሕዝቡ ክርስቶስን በመምሰል እያደገ መጥቷል ወይ? "እርሱ ሊልቅ፤ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።" (ዮሐ. 3፡30)

### ሠ. ለአገልግሎት መጠራት መመዘኛዎች:-

1. <u>በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ የጌታ ጸጋ በግልጥ ይታያል ወይ</u>?

እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች የማያቋርጥ የጌታ ጸጋ በውስጥ ሕይወታቸውም፥ በአገልግሎታቸውም ይታያል፤ ይፈሳል፤ የሌላ ሰው ሕይወትም ይነካል:: ንግግራቸውም ይሁን ጨዋታቸው፤ በውይይት መሃል፤ የሚናገሩትም ነገር ሁሉ በጸጋ የተቀመመ ነው:: ስብከታቸውም፤ ትምህርታቸውም፤ ጸሎታቸውም ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ እንዲያደንቁ ያደርጋቸዋል፤ የበለጠም በጽድቅ ለመኖርም ልባቸው ይጨክናል:: ለሰዎችም፤ ይልቁንም ለበደሉአቸውና ለጐዷቸው ሰዎች ይቅርታና ምሕረት ማድረግ ከጌታ የተሰጣቸው ጸጋ የተነሣ ዘወትር ይተጋሉ::

2. <u>ሌሎች ሰዎች በዚህ ሰው ውስጥ ያለውን ጥበብና እውቀት ለመቅዳት ይፈልጋሉ</u>?

የእግዚአብሔር ጥሪ እያላቸው ሰዎች በውስጣቸው የማይደርቅ የጥበብና የእውቀት ምንጭ ስላለ ብዙዎችን የማጠጣትና የመትከል ጸጋ አላቸው:: ከውስጣቸው የሚፈልቀው ጥበብና እውቀት የጠለቀ ከመሆኑም በላይ፥ የሰሙአቸው ሰዎች ሁሉ ይነኩበታል፤ ይታነፁበታል:: የሚናገሩት ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል የተለወሰና በጸጋ የተቀመመ ስለሆነና በቅንነትም ስለሚናገሩት፥ ሰው ሁሉ ያምናቸዋል::

3. <u>ይህ ሰው የሚኖረው መንፈሳዊ ኑሮው ያልተቆራረጠ (Consistent) ነው ወይ</u>?

የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች የሚኖሩት መንፈሳዊ ኑሮ የጸና፤ ያልተቆራረጠና የጓዳ ኑሮአቸው ከአደባባይ አገልግሎታቸው ጋር የሚጣጣም ነው:: በልባቸው የሚያስቡትና በአፋቸው የሚናገሩት ነገር አንድና ወጥ ነው:: (መዝ. 19:14) ሰው ቢያያቸው ባያያቸውም የትም ቦታና በየትኛውም ጊዜ ጽድቅና እውነት በማድረግ ወጥነት ያላቸው ሰዎች ናቸው:: የተደበቀ፤ የተለበጠ፤ ወይም የተሠወረ ነገር የላቸውም:: በብርሃን ለመመላለስ የቆረጠ ልብ አላቸው::

4. <u>የዚህ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ጥልቀት አለው ወይ? የእግዚአብሔር ቃል እውቀቱ፤ የፀሎት ሕይወቱ፤ ሲናገርም የሐሳብ ብስለት አለው</u>?

የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናትና ለጸሎት ብዙ ይተጋሉ፤ የጌታን ፊት ለማየት ናፍቆታቸው ነው:: ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ካላቸ

ው ሕብረት የተነሣ መናፍስትን የመለየት፥ ሰዎችም የተናገሩት ብቻ ሳይሆን ያልተ ናገሩትም ነገር የማድመጥ (Discernment)፤ በማንም ሰው አፍ ይነገር የእግዚአብሔር እውነት የሆነውን ለመስማትና ለመቀበል የሚችል ልብ አላቸው:: የሚናገሩትም ሐሳብ የተሰበጣጠረና የተበጣጠሰ ሳይሆን፤ ልቅም ያለ፤ እንደ ውሃ የሚፈስ፤ የነጠረ ና የበሰለ ነው::

5. ይህ ሰው በሰዎች መካከል በአድልዎ ይፈርዳል ወይ? ሰዎች ባላቸው የአገልግሎት ዓይነት፤ ባላቸው የኑሮ ቦታ (Status)፤ ዕድሜአቸውን በማየት ያደላል?

የእግዚአምብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ሰውን ሁሉ በጌታ ዓይን ስለሚያዩ ሁሉም በፊታቸው የከበረ ነው:: ሁሉንም በአክብሮትና በፍቅር የመያዝ ፀጋ ስላላቸው ያለምንም አድልዎ ማገልገል ይችላሉ:: በእግዚአብሔር ፊት የተለየ የሆነ ሰው የሌለውን ያህል፥ በእነርሱም ፊት የተለየ አቀራረብ የሚሰጡት ሰው የላቸውም:: ጌታ እግዚአብሔር በእነርሱ ቦታ ቢሆን የሚያደርገውን ማድረግ ይቀናቸዋል:: ሁሉንም በእኩልነት ማገልገልና ለሁሉም ሰው ፍትህ ማድረግ የዘወትር ውሳኔአቸው ነው::

6. ይህ ሰው በመከራ ውስጥ አልፎ ተፈትኖአል?

የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ጌታ ኢየሱስ "የሰው ሕይወት በእሳት ይቀመማልና" እንዳለው፤ በመከራ የተቀመሙ ናቸው:: በመከራ አልፈው የተፈተኑ ስለሆኑ ስብከታቸው፤ ትምህርታቸው፤ ንግግራቸውም ሳይቀር ልብን ይነካል:: ሰዎችንም ያፅናናል:: በመከራ አልፎ የነጠረና፥ ግርድፍ የሆነ ጥሬና ያልተነካ ሰው፥ አገልግሎታቸው አንድ አይደለም:: በመከራ የተቀመሙ ሰዎች ንግግራቸው ለዛ አለው፤ ስብከታቸው ሕይወትን ይነካል፤ ሕይወትንም ያመነጫል፤ የሰዎችም ልብ ከሚያልፉበት መከራ የተነሣ እንዳይወድቅም ተስፋቸውን ያድሳል::

7. ይህ ሰው ለአገልግሎት በመጠራቱ የሚያስከፍለውን ተምኖአል? ዋጋውን ለመክፈል በመስዋዕትነት ለማገልገልስ ፈቃደኛ ነው?

የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ድልድያቸው የተሰበረባቸው ሰዎች ስለሆኑ አገልግሎታቸውና ጥሪአቸው የሚያስከፍላቸውን ዋጋ ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ራሳቸውንም በመስዋዕትነትና በደስታ ያቀርባሉ እንጂ ከሚያገለግሉበት ቤተ ክርስቲያን ወይንም መንፈሳዊ ድርጅት ስለሚያገኙት "ደመወዝ"፤ ጥቅም ወይንም ስለሚወጡበት የሹመት እርከን ድርድር ውስጥ አይገቡም:: አገልግሎታቸውንም በገንዘብ አይተ

ምኑትም!!! የአገልግሎታቸውን ጥሪ ክብር ይጠብቃሉ:: ሐዋርያው ጳውሎስ "ተስፋ ችን፤ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? እናንተ ክብራችን ደስታ ችንም ናችሁና::" (1ተሰ. 2:19-20) እንዳለው የእርሱ ሽልማት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው::

1. የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ሰው ባያያቸው ብዙም የማይመስገኑና ያልተወሳሰቡ ቢሆኑም፤ ለእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚመቹ ጥራት ያላቸው ልዩ ስጦታዎች አላቸው::

2. የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች የጊዜ፤ የገንዘብ እና የስጦታዎች ባለ አደራ እንደሆኑና ጌታም በዓላማ እንደሰጣቸው ያውቃሉ::

3. የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ማንነታቸውን የሚያውቁ ከመሆናቸው ም በላይ የጠራቸውንና የታመኑበትንም ጌታ አጥልቀው ያውቃሉ::

4. የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ያልተቆራረጠ፤ የማይዋዥቅ፤ እና አቅጣጫ ያለው የኑሮና የአገልግሎት ዓላማ ያላቸው ናቸው::

5. የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው ሰዎች ለእግዚአብሔርና ለሕዝቡ የተሰጡ ስለሆኑ የአገልግሎታቸው ፍሬ ቋሚና ዝላቂነት አለው::

## ረ. የአገልግሎት ጥሪ የሌላቸው ሰዎች ባሕርያት:-

1. የእግዚአብሔር ጥሪ ሳይኖረው በአገልግሎት የተሠማራ ሰው አብዛኛውን ጊዜ የሚረካው ባከናወናቸው ጉዳዮች ላይ ነው:: ወደዚህ መሳካት የወሰደውን ሂደት ይህን ያህል አይገደውም::

2. የእግዚአብሔር ጥሪ ሳይኖረው በአገልግሎት የተሠማራ ሰው በሕልሙም በውኑም የሚያስበው በሥልጣንና በኃይል እርከን ላይ እንዴት እንደሚወጣና ሰዎች ንም ሆነ ነገሮችን እንዴት ቀጥጥሩ ሥር እንደሚያውል ነው::

3. የእግዚአብሔር ጥሪ ሳይኖረው በአገልግሎት የተሠማራ ሰው መጨረሻ በሌለው መስፋት፤ ትልቅነትና ስኬታማነት መረብ ውስጥ ራሱን ያጠላለፈና ከዚያም መውጣት የማይችል ነው::

4. የእግዚአብሔር ጥሪ ሳይኖረው በአገልግሎት የተሠማራ ሰው ለወጥነት ምን ም ግድ ስለማይለው የሕይወትም ይሁን የአገልግሎት ንፅህና የለውም:: የእግዚአብ ሔር ቤት ገንዘብና ንብረትም ለራሱ ጥቅም ለማዋል፤ ከትዳሩ ውጭ ለመማገጥና ከሌሎች አገልጋዮች ጋር በቂም በቀል ለመመላለስ ወደ ኋላ የማይል ሰው ነው::

ት የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲያገለግሉ እጅግ ይረዳቸዋል፡፡ የእግዚአብሔር ቤት ቅንዓት በብዙ ችግሮች ብናልፍ፣ ብዙ መከራ ብንቀበልም፣ ተስፋ የሚያስቆርጡ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙንም ቀጣይነት ያለው አገልግሎት ነገር ሁሉ ተፈትኖ የወጣ አገልግሎት እንድናገለግል ይረዳናል፡፡ ከዚህም ሌላ የእግዚአብሔር ሕዝብ ድካሙንና ጉስቁልናውን ሳናይ ጌታ ተስፋ ባልቆረጠበት ሕዝብ ተስፋ ሳንቆርጥ በመስጠትና በጥራት እንድናገለግለው ያደርገናል፡፡

ራዕይ ያለ ቅንዓት ደረቅ ነው፣ ሕይወት የለውም፣ ሕይወትም መስጠትን አይችልም፡፡ እንደዚሁም ቅንዓት ያለ ራዕይ ደግሞ የስሜት ግልቢያ ነው፡፡ ይዘት የሌለው ቅርፅ ብቻ፣ መልክ የሌለው ፎርም ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱም በጣምራ ሊያዙ ይገባቸዋል፡፡

## III. የአገልግሎት ራዕይ፡- (Vision)

### ሀ. የአገልግሎት ራዕይ ትርጉመ ወሰን፡-

- *"ራዕይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል፡፡"* (ምሳሌ 29:18)
- *"... ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራዕይ እምቢ አላልሁም፡፡"* (የሐዋ. ሥራ 26:19)

"ራዕይ ማለት ምናብን (Imagination) ተጠቅሞ ሁኔታዎችን አርቆና አጥልቆ የማየት ችሎታ፣ አሁን ያለውን ሁኔታ ማጤን (Insight) እና ወደ ፊት ሊሆንና ሊደረግ የሚገባውንም የማየት (Foresight) ችሎታ ነው፡፡ ራዕይ እየተደረገ ባለው ሁኔታና አሠራር አለመርካትና፣ ሊደረግ የሚችለውን አቅጣጫ ማየት ነው፡፡ ይህም ሁኔታ የጸድቅ ቁጣ በውስጣችን ይፈጥርና፥ የእግዚአብሔርን ፊት እንድናይ፣ ከእርሱም አዲስና መለኮታዊ ሐሳብ ተቀብለን በአዲስ አሠራር ነገሮችን አቅጣጫ እንድናስይዝ ያደርገናል፡፡"[74]

ራዕይ ማለት በአንድ ሰው ልብና አዕምሮ ውስጥ ስለ ወደፊት አካሄድ፣ አመራርና አሠራር ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ/ የሰረፀ ግልፅና ትኩረት ያለው መለኮታ

[74] John R. W. Stott, *Involvement: Social and Sexual Relationships in the Modern World*, (Old Tappan, NJ: Fleming H. Revell Company, 1984, 1985), 249. See also Greenleaf, *Servant Leadership*, 236.

ፂ ሐሳብ ነው። ራዕይ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ራስ፣ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብና ስለ ሁኔታዎች ልዩ መረዳትን በማግኘት ላይ የተመረኮዘ ነው።

◆ <u>ራዕይ በባሕርዩ ትጋትን፥ ጽናትን፥ የአገልጋይነት መንፈስንና ዲሲፕልን የሚጠይቅ በቁም ነገር ሊወሰድ የሚገባ ነገር ነው</u>!!!

**ለ. የራዕይ ባሕርያት:-**

1. ራዕይ እንደ ሰደድ እሳት ተላላፊ (Contagious) ስለሆነ የሕዝብን ልብ ያነሳሳል። (ነህምያ 2:17-18)
2. ራዕይ የትኩረት አቅጣጫ አለው። (ነህምያ 2:17)
3. ራዕይ ያላቸው ሰዎች ልባቸው የተሰበረ ነው።
4. ራዕይ የባለ ራዕዩ የግል አጀንዳን ያስጥላል።
5. ራዕይ መሪውን በትሕትና እንዲኖርና እንዲመላለስ ያደርገዋል።
6. ራዕይ መሪውን የበለጠ የእግዚአብሔርን ፊት እንዲያይና ወደ እርሱም እንዲቀርብ ያደርገዋል።
7. ራዕይ የመሪውን ልብ ሙሉ እንዲሆንና በእርግጠኝነት እንዲያገለግል ያደርገዋል። (ነህምያ 2:20)
8. ራዕይ መሪው ከለመደው ጎጆ፣ ሳጥን፣ አካባቢ እንዲወጣ ያፈርስበታል። ከተ ለማመደው በላይ አልፎ እንዲያስብ ያደርገዋል።
9. ራዕይ በሌሎች ሰዎች ዘንድ ዓይነተ ብዙ የሆነ ተቃውሞ እንዲነሳ ያደርገዋል። (ነህምያ 2:10፥ 19፤ 4:1-3፤ 7-8፤ 6:1-19)
10. ራዕይ ባለ ራዕዩን አልፎ ይኖራል!!!

**ሐ. የራዕይ ጥቅሞች:-**

1. ትልቅ ራዕይ መቀበል ከእኛ በላይና ያለፈ ስለሆነ በእግዚአብሔር ኃይል ሙሉ በሙሉ እንድንደገፍና እንድንታመን ያደርጋል።

2. ራዕይ ያለፈውን ዘመን ከአሁኑ ጋር እንድናገናኝ ስለሚረዳን የታሪክ ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንድናገለግል ይረዳል።

3. ራዕይ ቤተ ክርስቲያናችን አቅጣጫና ዓላማ ያላት እንድትሆን ያደርጋል።

4. ራዕይ ያለው ሰው ባለበት ቤተ ክርስቲያን የሕዝቡ ፍላጎትና መስጠት እየጨ መረና እያደገ ይመጣል።

5. ራዕይ ተቀባይነት ያለውና ቤተ ክርስቲያንን የሚያጎለብት ለውጥ እንዲመ ጣ ያደርጋል።

6. ራዕይ ቤተ ክርስቲያኒቱ አዳዲስ እዳሎቶችን ለማግኘት እንድትዘረጋና፣ በአቅሟ ሳትወሰን የራዕዩ ባለቤት የሆነው ጌታን ታምና እንድትወጣ ያደርጋል።

7. ራዕይ ለአዳዲስ ሐሳቦች፥ ምክሮች፥ ሕልሞች፥ እና ፈጠራዎች ልባችን የተከፈተ እንዲሆን ያደርጋል።

8. ራዕይ የወደፊት ብሩህ ተስፋ እንዲኖረን ያደርጋል።

9. ራዕይ በምንመራው ሕዝብ ልብ ውስጥ እርግጠኝነትን ይፈጥራል፣ ያነሣሣቸ ዋል፣ ለበለጠ መስጠትም ያበረታታቸዋል።

10. ራዕይ በመሪውም ሆነ፣ በሕዝቡ ልብ ውስጥ አጣዳፊነትን (Urgency)፣ እና ጥራትን ይፈጥራል።

11. ራዕይ የአገልግሎታችን ፍሬ እንዲበዛ ያደርጋል።

12. ራዕይ መሪው በብዙ ጸጋና ኃይል እንዲወጣ፥ በብርታትና በትጋትም እንዲያገለግል ይረዳዋል።

## መ. አብያተ ክርስትያናት ስለ ራዕይ ያላቸው አመለካከት:-

የራዕይ አቀባበል በተመለከተ አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ ደረጃ አላቸው። ከዚህ ጋር በተገናኘ አራት የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ መግለፁ አስፈላጊ ነው።

1. <u>አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች ራዕዩን ለመቀበል ይከዳሉ።</u> ራዕዩ እውነት እን ዳለው ያውቃሉ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ባህል አሠራር ወይም ልማድ በመያዝ፣ ወይ ከትዕቢት የተነሣ፣ ወይንም ክፉና ጠማማ ልብ ያላቸው መሪዎች ስለሆኑ ለመቀበል አይፈልጉም።

2. <u>ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ራዕዩን ሙሉ በሙሉ ከመቀበል ይልቅ አብሮ ጎን ለጎን እንዲሄድ (Co-Exist) እንዲያደርግ ያደረጋሉ።</u> እንዲህ ዓይነት አቀባበል ከይ ሉኝታ፣ ትችት ከመፍራት፣ ኃላፊነት ለመውሰድ ካለመፈለግ የሚመጣ "የጨዋ" ውሳኔ ነው።

3. ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ደግሞ ራዕዩን ሙሉ በሙሉ ይቀበሉታል፤ ሆኖም ግን ለራዕዩ መፈፀም ምክኒያት የሚሆኑ አስፈላጊ ለውጦችን ለማድረግ፤ ራዕዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ ራዕይ ለማድረግና በገንዘብ አቅጣጫ አስፈላጊውን ባጀት ለማውጣት አይፈልጉም።

4. ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ግን ራዕዩን ከመቀበላቸውም አልፈው፤ የቤተ ክርስቲያኒቱ ራዕይ እንዲሆን ያደርጋሉ። ከዚያም በላይ አስፈላጊውን የሰው፤ የገንዘብና የጊዜ ሀብት ሁሉ ከራዕዩ ጋር እንዲሄድ በጣም ወሳኝ የሆኑ በሥራ የሚተረጉሙ ቅጾችን ያወጣሉ። የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈልም ፈቃደኞች ናቸው። በጉልህ የሚታዩ ለውጦች እንዲመጡ ያደርጋሉ። ራዕይ ከግለሰቡ እጅ ተቀብለው የጋራ ራዕይ እንዲሆን ከራሳቸውም አልፈው፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በራዕዩ እንዲስማማና እንዲሠማራ ያደርጋሉ።

## ሠ. ራዕይ የሚደበዝዝባቸው ምክኒያቶች፡-

ከእግዚአብሔር የተሰጠን ራዕይ ሊደበዝዝ፤ ወይም ሊጠፋ፤ ካልተጠነቀቅን ደግሞ አቅጣጫውን ሊስት ይችላል። ራዕይ እንዲደበዝዝ ምክኒያት ከሚሆኑ ነገሮች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

1. በአመራር ላይ ያለው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የግንኙነት ሥምረት/ ጥምረት እየላላ ሲመጣና፤ መሪው ከራዕዩ ባለቤት ይልቅ ከራዕዩ ጋር እየተጣበቀና እያተኰረ ሲመጣ ይደበዝዛል።

2. መሪው ከመጠን በላይ ሲበካከንና በብዙ ነገሮች ውስጥ ሲገባ፤ በአገልግሎት ብዛት ሲወጠር፤ ቃሉን ለማጥናት ጊዜው እየቀጠነ ሲመጣ ብኩንነት (Burnout) ውስጥ ይገባል።

3. መሪው ወይንም አብረውት የሚያገለግሉ ሰዎች ደካማ አመራር ሲኖራቸው ራዕይ ይደበዝዛል።

4. መሪውና አብረውት የሚያገለግሉ ሰዎች ተጠያቂነት የሌለው አመራር በሚኖራቸው ጊዜ፤ ሕዝቡ ለራዕዩ መስጠትና መገዛት ሲያቅተው፤ የነበረውን ራዕይ ማናናቅ ሲጀምርም ራዕይ እየደበዘዘ ይመጣል።

5. መሪው ትዕግሥት ሲያጣና በወቅቱ ካጋጠመው ተግዳሮት የተነሣ ተስፋ ሲቆርጥ፤ ራዕዩ በራሱ ጊዜ የሚፈፀም ይመስል በሙሉ ኃይል ሲታገል፤ካልተፈፀመ ደግሞ ሲያኮርፍ ወይም መራራ ሲሆን ራዕይ እየደበዘዘ መምጣቱ አይቀሬ ነው።

6. መሪው ትኩረት ሲያጣ፣ ሁለገብ ሲሆን፣ በመንገዱ የመጣ ዕድል ሁሉ ሲወስደው፣ ሐሳቡ እንደተበላሸ ወተት ሲበጣጠስ ራዕይ ይደበዝዛል።

7. መሪው ነገርን ሁሉ ከራሱ ዙሪያና ከራሱ ክብር አንፃር የሚያይ መሪ (ego-Centric Leader) በሚሆንበት ጊዜ ጌታ ራዕዩን የሰጠው ለሕዝቡ ሲል እንደ ሆነ (ቆላ. 1:24-25) ረስቶ በትዕቢት ሲወጠር ሐዋርያው ጳውሎስ "የሆንኩትን የሆንኩት በእግዚአብሔር ፀጋ ነው።" ያለውን በመርሳት በራሱ ችሎታ እንደሚያገለግል ሲመስለው ራዕይ ከመደብዘዝም አልፎ ሊጠፋም፥ አቅጣጫውን ሊስትም ይችላል።

8. ለራዕዩ የሚገባ የቤተ ክርስቲያን አሠራር፥ ወይም መዋቅር፣ ወይም ውስጠ ደንብ፣ ወይንም የኑሮ ዘይቤ በማይኖርበትም ጊዜ ራዕይ ሊዳፈን ይችላል።

9. ከመሪውም ይሁን አብረውት ከሚያገለግሉ መሪዎች ሰዎች የመነጨ መጠላላት፣ መገፋፋት፣ አለመጣጣም፣ ደብዛው እየጠፋ ከቡድነኝነት መንፈስ የተነሣ መከፋፈል እየተተካ ይመጣል።

10. ራዕዩ ጊዜ ያለፈበትና በሌላ ራዕይ መተካት ሲገባ ወደ ልማዳዊ አሠራር ሲለወጥ፣ መሪዎቹ እየተደረገ ባለው ነገር ብቻ መርካት ሲጀምሩ የሕዝቡ ሕይወት ራዕይ ከማጣት የተነሣ ልቅ እና የሞራልና የሥነ ምግባር መለኪያ የሚጥስ ሕዝብ መሆን ይጀምራል።

## IV. የመሪዎች የማያቋርጥ ዕድገት:-

መሪዎች ይልቁንም የእግዚአብሔር ጥሪ ያላቸው መሪዎች የግል ሕይወታቸውን ሊያሳድጉ ቢፈልጉና ጥራትና ጥልቀት ያለው አገልግሎት ለማገልገል የጨከነ ልብ ካላቸው በሚከተሉት ዋና ጉዳዮች የተጨበጠ እና በሥራ ሊተረጎም የሚችል የዕድገት ፕላን እንዲኖራቸው በትህትና አሳስባለሁ።

### ሀ. የመንፈሳዊ ዕድገት ትኩረት:-

እግዚአብሔር የጠራቸው መሪዎች በየጊዜው የማያቋርጥ ዕድገት እንዲኖራቸው ከፈለጉ በግል ሕይወታቸው፣ ይልቁንም በመንፈሳዊ ዕድገት ላይ ያተኮረ ዕቅድ ሊኖራቸው ይገባል። የጨከነ ጥናት እና ትጋት የተሞላው በሆነ መንገድ መፅሐፍ ቅዱስ ለማጥናት የሚረዳቸው የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ (Inductive Bible

Study)፣ የመጽሐፍ ቅዱስ አሰሳ (Bible Survey) እና የጥሞና ጊዜ (Bible Meditation) እንዲኖራቸው እመክራለሁ:: በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜም ርዕሳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የባሕርያት ጥናት፣ ጠቅለል ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (Deductive Bible Study)፣ እና ዝርዝር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (Inductive Bible Study Method) ማለትም በአማርኛ:- "መስተጋብአዊ ሥነ አምክንዮ" መንገዶችን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ቃል በጥልቀትና በትጋት ሊያጠኑ ይችላሉ:: ከዚህም ሌላ በእግዚአብሔር ፊት የሚያሳልፉትም የጸሎት ሕይወታቸው ትርጉም ያለው፣ ጥልቀትና ዓላማያለውና ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚመጣ እንዲሆን ውስጣዊ ጥማት ማሳደግ አለባቸው::

### ለ. በግንኙነት ሥምረት ላይ ያተኰረ ዕድገት:-

እግዚአብሔር የጠራቸው መሪዎች ከሰዎች ጋር ያላቸው የግንኙነት ጥምረት ትርጉም ያለው፣ ግላዊና ልባዊ የሆነ እና የሚደግፍ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሕይወታቸው ዓላማ ሊያደርጉት ይገባል:: የግንኙነት መሥመሮችንም መፍጠሩም በጣም አስፈላጊ ነው:: ከግንኙነት ሥምረት ጋር በተያያዘ መልክ መሪዎች ሁሉ አራት ዓይነት ሰዎች እንዲኖሩአቸው እመክራልሁ:- <u>የልብ ጓደኞች፣ በቅርብ የሚከታተሏቸው መሪዎች</u> (Coaches)፣ <u>በጥልቀት የሚያሳድጓቸው መሪዎች</u> (Mentors)፣ <u>እና ድጋፍ የሚሰጥ የቤተሰቦች ቡድን</u> (Support Group)!!!

### ሐ. በተጠያቂነት ላይ ያተኰረ ዕድገት:-

በእግዚአብሔር የተጠሩ ሰዎች ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ፊትና በሌሎች ሰዎች ፊት (ማለትም በሌሎች መሪዎችና በሕዝቡም ፊት ግልፅነትና ሐቀኝነት ያለው ሕይወት (Transparent)፣ ኑሮና አገልግሎት እንዲኖራቸው የነጠረና በየጊዜው ሊቀመጡ ምክር፣ ሐሳብና ቢያስፈልግም ተግሣፅ ሊቀበሉ ይገባቸዋል::

### መ. በወጥነት ላይ ያተኰረ ዕድገት:-

በእግዚአብሔር የተጠሩ መሪዎች የሕይወታቸውን ንፅህና ለመጠበቅ በራሳቸው ላይ ሊጨክኑ፣ ምላሳቸውን በጥርሶቻቸው መካከል ሊነክሱና የቅድስና ዲሲፕሊን እንዲኖራቸው እንደ ኢዮብ ከዓይናቸው ጋር ቃል ኪዳን ሊገቡ (ኢዮብ 31:1-15) ያስፈልጋቸዋል:: ሐዋርያው ጳውሎስ "ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው

ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ።" (የሐው. ሥራ 24፡ 16) እንዳለው በጌታ የተጠሩ መሪዎች ዓላማ ሊሆን ይገባዋል ብዬ አምናለሁ።

### ሠ. የተጠሩ መሪዎች የግል መመዘኛ፡-

1. በውስጣቸው ያለው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተሟጠጠ እንዲሄድ የሚያደ ርግ የግል መንፈሳዊ ሕይወት ቀጸጸ እንዲኖር መጠንቀቅ።

2. የረካ ሰው ለማሆን፤ ለለውጥ፤ ለፅናት እና ለለውጥ ሂደት መስጠታቸውን ማረጋገጥ።

3. ምንም ጊዜ በየደረጃው የሕይወታቸውና የአገልግሎታቸውን ተልዕኮ መከለስ ግምገማ ማካሄድ።

4. በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በእግዚአብሔር ፀጋ ያላቸውን እምነትና ድጋፍ በየጊዜው መገምገም።

5. አስቀድሞና አርቆ ማየት የሚችል ልብና መንፈስ እያደገ መምጣቱን ማረጋ ገጥ። እንደ ሰጎን ጸተኛ መሪ (Passive) ነኝ? (ኢዮብ 39፡13-18)፤ ወይስ እንደ ፈረስ የሚንደፋደፍ መሪ (Reactive) ነኝ? (ኢዮብ 39፡19-25)፤ ወይንስ ደግሞ እንደ ንስ ር አርቆ ማየት የሚችል መሪ (Proactive) ነኝ? (ኢዮብ 39፡26-30) ብለው ራሳቸው ን መጠየቅ?

6. የትኩረታቸው አቅጣጫ ከብዛት ይልቅ፤ ጥራት ላይ መሆኑ መገምገም።

7. አገልግሎታቸውም የሚያጠራጥሩና የማይታመኑ ከመሆን ይልቅ፤ እውነትን የተሞሉ፥ የሚታመኑና፥ እርግጠኝነት ያላቸው (Authentic) መሆናቸውን በየጊዜ ው ማጣራት።

8. እግዚአብሔር የጠራቸው መሪዎች "የሰዎች ክቡርነት" "የማገለግለው የጉባ ዔውን ክብር" "የሰዎችን አስፈላጊነት" እምንበታልሁ ወይ? ብለው ራሳቸውን መጠየቅ።

9. ባላቸው የእግዚአብሔር ቤት በቅንዓትና በራዕይ መሃል ሚዛናቸውን ጠብቀ ው ለመያዝ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

10. በእግዚአብሔር የተጠሩ መሪዎች የእግዚአብሔር ሀላዎት ልዩ ሀብታቸው እንደሆነ በማስተዋል መያዛቸውን በየጊዜው ራሳቸውን መመርመር።

11. እግዚአብሔር በአመራር ላይ እንዲቀመጡ የፈቀደላቸውን የመሪነት ሥፍራ፥ የጥሪ ክብር፣ የጥሪው አድማስ፣ የጥሪው ስፋት፣ እና ጥሪው የሚያስከፍለውን ዋጋ መረዳታቸውን ማስረገጥ።

12. እግዚአብሔር የጠራቸው መሪዎች በስብከታቸውም ሆነ በትምህርታቸው "ለተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛ ነኝ?" (AM I TRUE TO THE TEXT?) ብለው አጥብቀው መጠየቅ። በተጨማሪም "ታሪክን ማንበብ፣ ማጤንና መተርጎም እችላለሁ ወይ? የታሪክንም ሂደት አቅጣጫ አስተውዬ እግዚአብሔር ሊሠራ ካለው ትልቁ ዓላማ ጋር ማገናዘብ እችላለሁ ወይ? ብለው ራሳቸውን መጠየቅ ይገባቸዋል።